<u>አባባሽ መርገፉ</u>

ጭር ባለው መንደር ሌት በጠፍ ጨረቃ
አሰበ ተፈሪ - አቃቂ በሰቃ
ምድር - አዲስ አበባ ፒይሳና መርካቶ
ጭንቅላትሽ ፈርሶ ሆድሽ ተሰዝቶ
ጥርሶችሽ ዕረግፈው ዐይንሽ ተጎልጉሎ
ጎጃም ክ/ሀገር ጎንደርና ወሎ
ሀረር - ድሬዳዋ መንገድ ላይ ተጥሎ
ቅሬትሽ ሲታፈስ ሰውነትሽ ፈርሶ
ደምሽ ተንዠቅዥቆ አፈሩን አርሶ
ዕዳሽን ሲከፍል ሬሳሽ ተሸጠ
ሀዘንሽ በዘፈን ሙሾው ተለዉጠ
ዕለቅሶው ሽብሽባ ዋይታው እስክስታ
ይህ ነበር ያንቺው ሠርግ ለቀረው ትውስታ!

በአብዮት ማዕበል ለትግል ተነስተሽ
የማይፈታ ህልም ራኢይ አንግበሽ
የማይድን በሽታ አክማለሁ ብለሽ
አጥንትሽ ተለቅሞ ከሰውነት ወተሽ
ዕቱ የዕድሜ-ድሃ አፈር ውስጥ ያረጀሽ
የዚያ ትውልድ ፈርጥ ዐይን ላይ የበቀልሽ
ትግልሽ ለማን ነበር ድል መቀናጀቱ
ትንሳኤው ብሥራቱ
ለባንዳው ልጅ ነበር የንጉሥ አፍቅሬ?
ወይስ ለኢሰፓው ለፋሽስቱ ካድሬ
እያረጉ ላሉት ሞትሽን ሞተ-ከንቱ
ለጠባቦች ነበር ወይስ ለትምክህቱ?
ባጭር ተቀጭቶ አፈር ውስጥ ማርጀቱ
እኮ ለማን ነበር ሞትሽ ቤዛነቱ?

አንቺስ ዕቱ ዕመቤት
አሲምባና ፀለምት
በረሃ ያለሽው አጅሬ ጃኖራ
አዳኝ አገር ጨቆ-አርማጭሆ-ቋራ
መልዛ መቀጠዋ ሰሜን ጃንአሞራ
መተክል በርሃ በለሳ ያለሽው
ላንድ ክንድ ጉድጓድ ላፈር ያልበቃሽዉ
አፅምሽ ተከስክሶ ቀርቶ በርሃ ላይ
ሌሊት ሌሊት ውርጩ ቀን ቀን ደግሞ ፀሐይ
ሲፈራረቁበት ስቃይ እንግልቱ
ለማን ነበር ሞቱ መስዋዕትነቱ?
ምን ብሎ ዘከረው ታሪክ በምዕራፉ
እኮ ለማን ነበር አበባሽ መርገፉ?

አንቺስ ያገር ቤቷ ከልታማዋ እህቴ
ያጥንቴ ስባሪ ግማሽ ሰዉነቴ
አረሙ ጉልጉሎው ወፍጬውና መጁ
ማብሰል መቀቀሉ የሙቀጫ ልጁ
ቤት ማበጃጀቱ ፈትሉና ስፌቱ
ዉኃ በማድጋ ከወንዝ መቅዳቱ
ከዕርግዝና በላይ ልጅ አዝሎ በጀርባ
ተውቦ መታየት ቁንጅና ደርባባ
አለ ዕድሜ ጋብቻሽ አበባሽ መርገፉ
ዕቴ እሴትነትሽ በድሎሻል ግፉ!!

መድሎው የተፈጥሮ ድርሻሽ የመክሊቱ
አስረዘመው መሰል ቀኑን ከሌሊቱ
ነዶ ነዶ አለቀ ያ ሻማሽ መብራቱ !!

መጋቢት 1999
አብርሃም በየነ (ከአትላንታ)